# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

**በአዲስ አበባ የኢሕአፓ የቅስቀሳ ወረቀቶች ተሰራጩ**

ኢሕአፓ ለሕዝባዊ አመጽ እያደረገ ያለውን ሰፊ ቅስቀሳ በመቀጠል ዓርብ ዕለት በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ልዩ ቦታዎች የቅሰቀሳ በራሪዎችን አሰራጭቷል። ዓርማውን የያዙና ሕዝባዊ ትግላችን ይፋፋም የሚል መልእክቶችን ያዘሉ ቢጫ ተለጣፊዎችንም በየቦታው ለጥፏል። ለመጀመሪያ ጊዜ በውስጣቸው የኢሕአፓ መልእክቶችን ያያዙ ባለልዩ ቀለም ፊኛዎችንም ወደሰማይ ለቋል። (የጥቂቶችን ፎቶዎች ከታች ይመልከቱ)።

ይህ የስርጭት እርምጃ የተካሄደው በአዲሱ ገበያ ፤ ጊዮርጊስና ፒያሳ፤ በአራት ኪሎና ቀበና በየካ፤ ሾላ፤ መገናኛና ገርጂ፤ በሃያ ሁለት ኮልፌ፤ ሰፈረ ሰላምና አዲሱ ሚካኤል፤ አውቶቡስ ተራና ባንኮ ዲሮማ በመርካቶና በቅሎ ቤት ወዘተ... ነው። በየመንገዱም መልእክቶች ተቀምጠዋል። በልዩ ልዩ ቀለም የተሰራጩት መልእክቶች ወያኔ በግድብ ግንባታ ሽፋን የጀመረውን ዝርፊያ የሚያወግዙ፤ ለአመጽ የሚጠሩና የሚቀሰቅሱ ጽሁፎች ናቸው ። ፊኛዎቹ ሲፈነዱም በውስጣቸው ያሉት በራሪዎች ተሰራጭተዋል።

ኢሕአፓ በትግሉ መስክ እንተባበር ማለቱን የቀጠለ ሲሆን በራሱ መስራት ያለበትን በተመለከተ ግን እየተንቀሳቀሰና ለወሳኙም ፍልሚያ ሕዝብን እየጠራና እያደራጀ መሆኑንም ገልጿል።

በሕዝባዊ አመጽ ሕዝቡ ድልን ይቀዳጃል።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል



**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com